

# አስራ ሁለቱ ሰላዮች

* እግዚአብሔር ሙሴን የከነዓንን ምድር ይሰልሉ ዘንድ ሰላዮችን እንዲልክ አዘዘው። የሚልካቸው ሰላዮችም ከእያንዳንዱ የእስራኤል ጎሳ የተወከሉ መሆን እንዳለባቸው ይነግረዋል። ስለዚህም ስለምድሪቱና በምድሪቱ ውስጥ ስላሉ ሰዎች አጥንተው እንዲመጡ አስራ ሁለት ሰላዮች ተላኩ። ሙሴ በተጨማሪም የምድሪቱ ሰዎች ብርቱ ወይንም ደካማ እንደሆኑ አይተው እንዲመጡ ነገራቸው። በከተሞች እንደሚኖሩ ወይንም በድንኳን ውስጥ እንደሚኖሩ ማረጋገጥም ከሰላዮቹ ተልእኮ አንደኛው ነበር። በተጨማሪም የምድሪቱ ፍሬ ምን እንደሚመስልና ደን እንዳላቸውም ማወቅ እንደሚፈልግ ሙሴ ለሰላዮቹ ነገራቸው። ስለዚህ የምድሪቱን ፍሬ ይዘው እንዲመጡ አዘዛቸው።

*. ሰዎቹም ወደምድሪቱ ሄደው ምድሪቱ እጅግ መልካም እንደሆነች አይተው መጡ። ያመጧቸው ፍሬዎች እጅግ ትልቅ ከመሆናቸው የተነሳ በእንጨት አድርገው ሁለት ሰዎች ነበር የተሸከሙት። ነገር ግን በምድሪቱ የነበሩት ነዋሪዎች ግዙፍ ከመሆናቸው የተነሳ አብዛኞቹ ሰላዮች በፍርሃት ተሞሉ። ምድሪቱንም ሲሰልሉ ለ40 ቀናት ቆዩ።

* ወደ ድንኳኖቻቸው ሲመለሱም ለሙሴ ይዘዋቸው ያመጧቸውን የምድሪቱን ፍሬዎች አሳዩት። ከሰላዮቹ አስሮቹ ስለ ነዋሪዎቹ ግዙፍነትና እንዴት አስፈሪዎች እንደሆኑ ማውራት ጀመሩ። እንዲሁም በግንብ ስለተከበቡ ትልልቅ ከተሞችም አወሩ። “ወደከተሞቻቸው ድርሽ ማለት አንችልም፤ ምክንያቱም በእነርሱ አይን እኛ እንደአንበጣ ነን።” አሉ።

ካሌብና ኢየሱስ ግን “እንሂድ ምድሪቱን እንውረስ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ እናሸንፋቸዋለን።” አሉ።

* እስራኤላውያን እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ እንዳሰበላቸው የከነአንን ምድር ሳይወረሱ ቀሩ። ከዚህ የተነሳም እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለአርባ አመታት እንዲንከራተቱ በማድረግ ቀጣቸው። ሰላዮቹ በከነአን ምድር በቆዩባቸው ለአርባ ቀናት ለእያንዳንዲቱ አንድ አመት በበረሃ ተጓዙ።

. ከአስራ ሁለቱ ሰላዮች ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ ወደከነአን ምድር የገቡት።

የአስራ ሁለቱ ሰላዮች ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በዘኍልቁ መፅሐፍ በምዕራፍ 13 እና በምዕራፍ 14 ውስጥ ይገኛል።